# <u>እሾክን በእሾክ</u>

*ከቀመሩ ደሳለኝ*

አሸባሪ እያሉ ሽብር ቀፈቀፉ ፣
ውሸት አንባንሮ እየቀጣጠፉ ፣
የወራሪ ዓላማ ምኞትን ሊያሳኩ ፣
በእጅጉ ዝርፊያውን አገርን ሊያውኩ ፣
አሸባሪ ወያኔ፣ አንተ አገር ሕዝብ የጠላህ ፣
ብትቆርጥ ብትቀጥል ከንቱ ነው ውዳሴህ ፣
አጉል ነው ድካምህ አሸባሪ አለብህ ፣
ሕዝብ ስትበድል ዝም ብሎም አያይህ ፣
እሾክን በእሾክ ብሎ ህዝብ ተነሣብህ ፣
ከዚህ ላይ አለቀ ከመቃብር ገባህ።

አሸባሪ ላሉ አሸባሪዎች አሉ ፣
ለአገር ወገን መብት ፅኑ የሚታገሉ ፣
ጠላት አሸባሪን መዘው የሚጥሉ ፣
ጀግና ልበ-ሙሉ ሰው አገር የሚሉ ፣
ሕገወጥ ሰዎችን ሕገ-ወጥ የጠሉ ፣
ለኢትዮጵያ አንድነት በቅጥ ያስባሉ ፣
ክንድን አስተባብረው ነፃ ያወጣሉ።

ለአሸባሪው ሽብርት ቢሆን ምናለበት ፣
ለአገር ዋስትና ለሕዝብ መብት ኩራት ፣
ሰይፍን የመዘዙ በሰይፍ ይመታሉ ፣
ይላል በተፈጥሮ፣ ይላል አሪት ቃሉ።
ቢቆጡህ መቆጣት፣ ሲመቱህ መምታት ነው ፣
ቢሰድቡህም መስደብ ቢከሱህ መክሰስ ነው ፣
አገር ጥሎ መሄድ ለጠላት ማስፋት ነው ፣

አሸባሪ ጠላት ወያኔ ማፊያው ፣
አሸባሪ እሱ ነው እናስወግደው ፣
ሌላም እንዳይተካ ሥሩን ንቀለው ፣
ይጥፉ ካገር ይውጣ ትምህርት ይሰጠው ፣
አስወግድ ተባይን በህብረት በመላ ፣
እንዳያነቅዝብህ ውስጡ እንዳይበላ ፣
ተነቃቅሎ ይውጣ ሽንኮፉ በሞላ።

አልቆጣ ብለህ ኩሶ እንደመረረ ፣
እንባህን ጠጥተህ ውስጥህ እያረረ ፣
ደስታህ ውስጥ ታች ዘቅጦ ቀረ።
ዝም በል ስትባል አንገትህን ደፋህ ፣
ደካማ ትንሽ ሰው ሆነህም ተገኘህ ፣
አገር- ሃብት፣ ንብረትን፣ መሬትህ ተነጥቀህ ፣
አሸባሪም ብለው በሽብር ከሰሱህ ፣
ፍርሃትህን ጨርስ ከዚህ ላይ ግታቸው ፣
አሸባሪ ሆነህ አንተም አሳያቸው ፣
በመጡበት መስመር ከዚያ ስደዳቸው ፣
በቆፈሩት ጉድጓድ በዚያው አስቀራቸው።

ያገር ሰው ወይ በለኝ የትነው የምትኖረው ፣
አገርህ ተወራ ወዴት ነው ያለኸው ፣
ዳር ድንበር ተደፍሮ ሕዝብ ወገን ተዋርደው ፣
ሃብት ንብረታችን ቅርስ ሁሉ ተዘርፈው ፣
ጭቆና፣ መከራ፣ ግፍ ቀንበርን አዝለው ፣
በደዌ በሽታ በርሃብ ሰውን ፈጀው ፣
አስረው፣ ገረፈው ከሀገር አሳድደው ፣
አሸባሪ እያለ በእጅጉ በደለው ፣
ወያኔ አገር ወርሮ መሬትህን ሸጠው ፣
ያገር ሰው አለሁ በል ወዴት ነው ያለኸው ፣

እየፈለገችህ እናት ሰው እናት ሰው ፣
ኢትዮጵያ ጠራችህ ብላ ልጄ ጀግናው ፣
ቶሎ ድረስላት ጀግና ሰው አርበኛው።

አትሁን ተላላ ምንድነው ዝምታ ፣
አገሩ ያንተ ነው ጧትም ሆነ ማታ፣
ችላ በማለትህ ሁሉን እንደ ደስታ ፣
ዘረፋንም ቀሙን አረጉን ወስላታ ፣
ትግሥታችን ይሁን ከዚህ ላይ ይገታ ፣
ተነሳ ተቆጣ ክንድህን አበርታ ፣
መንግለህም ጣለው ወያኔ በሽታ ፣
ጠላት፣ አሸባሪን ፈንቅለው በእርምታ ፣
አገር ነፃ ትሁን ለትውልድ አለኝታ ፣
አንተም ኑር በተስፋ ኮርተህ በደስታ።